ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በጀርመንና በአሜሪካን ድምፅ ራዲዮ የሰጡትን ቃለ ምልልስ አስመልክቶ ከኢትዮጵያ የተላከ

ጥቅምት 23 ቀን 2000 ዓ/ም

ሻቱሌ፤ ከቦሌ

# ለድል አጥቢያ አርበኝነት ማ ማንን ተጠጋ?

ይህችን አጠር ያለች አስተያየት ለመሰንዘር የተነሳሁት፤ በቅርቡ ከእስር በተለቀቁት የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ከፍተኛ የአመራር አባላት መካከል ተፈጠረ የተባለው አለመግባባት አሳዝኖኝና አስገርሞኝ ነው። ነገሩ እኮ! የሆነው "ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጢጥ" እንደተባለው ነው። በነገራችን ላይ፤ የዚህ አስተያየት ፀሐፊ የየትኛውም አፈንጋጭ ወገን አለመሆኔን በአክብሮት እገልጻለሁ፤ ከዚሁ ጋር አያይዤ ስለማንነቴ፤ በእግረ መንገድ አንድ ሁለት አረፍተ ነገር ላስፍር።

በሙያ ጋዜጠኛ ነበርኩ። የኢትዮጵያን ሕዝብ የልብ ትርታ አዳምጠው፤ ብሶቱን ብሶታቸው አድርገው ተነስተው የነበሩትን የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሙያው የሚጠይቀውን ሚዛናዊነት ጠብቀው ሲያበረታቱና በዋጋ የማይለካ መስዋዕት ሲከፍሉ ከነበሩት አንጋፋ የግል ነፃ ፕሬስ ተቋማት ውስጥ ሥሠራ ነበር። ከግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ/ም ብሔራዊ ምርጫ ማግሥት፤ በወያኔ-ኢህአዴግ መንግሥት ትዕዛዝ (አፈና)፤ ነፃው የኢትዮጵያ ፕሬስ ታግዶ፣ ንብረታችን በመንግሥት የደህንነት ጅቦች ከተመዘበረ በኋላ ብዕሬን እንደ እኔው ጡረታ አስገብቻት ነበር። ወደ ተነሳሁበት ርዕሰ ጉዳይ ልመለስና፤ ሁላንም ከፍተኛ የቅንጅት የአመራር አባላት አንድ ጥያቄ ልጠይቅ፤

የኢትዮጵያን ሕዝብ በ3000 ዘመን ታሪኩ ለመጀመርያ ጊዜ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ባደረገው የግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ/ም ታላቅ ምርጫ ውጤት መሠረት፤ የመንግሥት ሥልጣኑን በሰላማዊ መንገድ ተረክባችሁ ቢሆን ኖሮ እንዴት አገሪቱን ልትመሩ ነበር?

ልብ በሉ፤ ወያኔ-ኢህአዴግ በምርጫው በዝረራ ከጫወታ ውጭ መሆኑን አምኖ፤ በተቃዋሚነት እናንተ በመንግሥትነት ተሰይማችሁ ቢሆን ኖሮ፤ ልደቱ አያሌውም ወደ ወያኔ ጎራ ከመኮብለል ከእናንተው ጋር ይቆይ ነበር። ታዲያ እነ ብርቱካን በአንድ በኩል፣ እነ ልደቱ በሌላ በኩል፣ እነ ኢንጂነር ኃይሉ በሦስተኛ በኩል ሆናችሁ አገሪቱን እንዴትና ወዴት ልትመሯት ነበር?

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፤ በቅርቡ ለአሜሪካ ድምፅ የአማርኛው አገልግሎት በሰጡት አስተያየት፤ ጠቡ የመነጨው ከሥልጣን ጥመኝነት እንደሆነ ተናግረዋል። ይህን ሲሉ፤ የቅንጅት ከፍተኛ የአመራር አባላት ቀድሞውንም ቢሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዘመናት የግፍና የጭቆና ፋሺስታዊ አገዛዝ ነፃ የማውጣት ተልዕኮ ሳይሆን በወያኔ-ኢህአዴግ እግር የመተካት ዓላማ አንግበው ነው የተነሱት ማለታቸው ነው? ፕሮፌሰሩ ክሳቸውን በማስረጃ ለማንጠር አለመቻላቸው ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል።

በሌላ በኩል የቅንጅትን ውህደት ከመሠረት ወደ እድገት ለማሸጋገር ግንባር ቀደም ተሰላፊ ከነበሩት መካከል አንዱ እርሳቸው (ፕሮፌሰሩ) ነበሩ። ይህንን ድብቅ የሥልጣን ጥመኝነት በወቅቱ፤ ማለት ገና ከውጥኑ ለመገንዘብ አለመቻላቸው በእርሳቸው በኩል የነበረውን ድክመት የሚያመለክት ይመስለኛል።

እነ ልደቱ፣ እነ ብርትካን፤ ከመኢአድ (ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት) ጋር ውህደት ወይም ግንባር እንፍጠር በማለት ሲጠይቁ የነበሩት "ትንሽ አሻሮ ቋጥረው ከእንቅብ ሙሉ ቆሎ ጋር ለመደባለቅ ነበር" የሚል እንድምታ ያለው ይመስላል የፕሮፌሰር መስፍን ማጋለጥ። ይህን የሚሰኘው መኢአድ ከአንድ ሚሊዮን በላይ አባላት ያሉት፣ በመላው የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች ጽ/ቤት የነበሩት፤ በአንጋፋነቱም የታወቀ የፖለቲካ ድርጅት ስለነበር ከእርሱ ጋር መደባለቅ ወደ መንግሥት ሥልጣን ያደርሳል ተብሎ የታሰበ ይመስላል። ካለዚያ ኢንጂነር ኃይሉና ቡድናቸው የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት መኢአድን ብቻ ይዘን ከወያኔ-ኢህአዴግ ጋር መወዳደር ፓርላማ አያስገባን ይሆናልና በእነዚህ ለጋ የፖለቲካ ድርጅቶች መታጀብ ያስፈልገናል የሚል አቋም ይዘው ነው ቅንጅትን ለመፍጠር የሞከሩት ብለን ማመን ይኖርብናል።

በሌላ አባባል የቅንጅትን አፈጣጠር ከሥልጣን ጥመኝነት ጋር አያይዘን እንመልከተው። ቅንጅትን የመፍጠር ጥያቄ በመጀመርያ ከየት መነጨ? መሐመድ ወደ ተራራው ሔደ ወይስ ተራራው ነው ወደ መሐመድ የሔደው? ማን ማንን መማርያ አድርጎ ነው የሥልጣን ጥማቱን ለማርካት የሞከረው? "ጅብን ሲወጉ፤ በአህያ ይጠጉ" እንደተባለው የሆነበትን ጉዳይ፤ አንዱ የሌላው የሥልጣን መረማመጃ እንዲሆን እንደተፈለገ፤ ክቡር ፕሮፌሰር መስፍን ፍርጥርጥ አድርገው ሊነግሩን ይገባል። እኔ በበኩሌ የጅምላ ክሳቸውን መቀበል ያስቸግረኛል።